## • ሠላምና ብሔራዊ ዕርቅ በኢትዮጵያ ለውይይት የቀረበ

### መግቢያ

በአገራችን የረዥም ጊዜ የህዘቦች ታሪክ የኢትዮጵያ ህዝቦች ፍትህ-ዕኩልነት- ዴሞክራሲና ሠላም እንዲሰፍን ይህ ነው የማይባል ታላቅ መከራና ክቡር መስዋዕትነት የከፈሉባቸው ሠላሚዊና የአመፅ እንቅስቀሴዎችን አካሂደዋል ፡፡
ከላመታደል ግን አገራችን ዛሬም ሠላም ፍትህና ዴሞክራሲ የሰፈነባት- በልማትና በዕድገት ጎዳና የምትራመድ አገር አልሆነችም፡፡ ለዚህም በርካታ ምክንያቶች ቢኖሩም እንደ ዓቢይ ምክንያት ተደርጎ የሚቀርበው የህዝብን ይሁንታን ያገኘ ፥ ህዝብን በእኩልነት የሚዳኝ፥ ህዝባዊና ዴሞክራሲያዊ የሆነ መንግሥት አለመመሥረቱ፥ አገርና ህዝብ የሚተዳደሩበት ዴሞክራሲያዊ ህገ-መንግሥት አለመኖሩ ነው ፡፡ እስከዛሬ በተጨባጭ እንደታየው በኢትዮጵያ ህዝብ ጫንቃ ላይ የተፈራረቁበት ገዥዎቹ በየበኩላቸው አንዱ ከሌላው የሚለዩበቻው ባህርያት ቢኖሯቸውም ሁሉንም ግን አንድ የሚያስመስሏቸው በህርያትም አሏቸው ፡፡ እነሱም ሁሉም በኃይል ሥልጣን መያዛቸው ፥ አምባገነነንታቸው፥የከፋፋለህ ግዛ ፖሊሲ ማራመዳቸው፥ በህዝቦች መካከል የጋራ መተማመንና ከበሬታን ለመፍጠር፥  ሁሉም ዘላቂ ሠላምና መረጋጋትን በአገሪቱ ውስጥ ለማስፈን አለመቻላቸው ደግሞ ዛሬ ለሁሉም በግልጥ እየታየ ያለ ነው፡፡ በዚህም የተነሳ በአገራችን ለብሔራዊ ክብርና ነፃነት፥ ለዴሞክራሲ፥ለማህበራዊ ፍትህ፥ ለሠላምና ለዕኩልነት የሚታገሉ ኃይሎች የሠላማዊ ለውጥ በሮች ስለተዘጉባቸው የአመፅን ጎዳና እንዲከተሉ የሚጋብዝ በር ተቀዶ ይገኛል.፡፡
የአሄው አገዛዝ ለተለዋዋጩ የአገራችን የፖለቲካና ማህበራዊ ዕውነታ ተገቢውን መልስ ለመስጠት አለመሞከሩ፥ ህዝብን ያሳተፈ ዴሞክራሲ እንዲመጣ ለተደረገው ትግልና ለቀረበው የህዝብ ጥያቄ የዝሆን ጆሮ ይስጠኝ ማለቱ፥ ለብሔር /ብሔረሰብ ዕኩልነት ደንታ ቢስ መሆኑ፥ የመሬትንሥርዓት ለማሻሻል አለመፈለጉ፥ የኃይማኖት ዕኩልነትን አለማረጋገጡ፥ የትምህርት ሥርዓቱን ለአገሪቱ ልማትና ዕድገት በሚጠቅም መልኩ ከመቀየር ይልቅ አገርንና ትውልድን በሚጎዳ መልኩ ሴክተር ሪቪው የተሰኘውን ሥርዓት ትምህርት በመቅረፁ፥ ወዘተ የተነሳ የመደብ ቅርኔው በኅብረተሰቡ ውስጥ እንዲያድግና እንዲከር፥ በተለያዩ የአገሪቱ ክፍሎች ውስጥ የተበታተኑ የሽፍትነት ባህሪ ያላቸው በዝቅተኛ ደረጃም ቢሆን የተደራጀን መልክ የያዙ የአመፅ እንቅስቀሴዎች እንዲስፋፉና ሁኔታዎች እንዲፈጠሩ ተደርጓል፡፡ በተለይም በአገሪቱ ሰሜናዊ፥ምስራቃዊና ደቡባዊ ክፍሎች ተበደልን፥ተረገጥን፥ የሚሉ ብሔር/ብሔረሰቦች በትጥቅ የተደገፈ እንቅስቃሴ በማድረግ፥ ከኃይለሥላሴ አገዛዝ ጠባቂዎች ጋር መጋጨታቸው ሥርዓቱ በቅራኔዎች የተሞላ መሆኑን

ያረጋግጣሉ ። በመጨረሻም ይህ ያረጀና ያፈጀ አገዛዝ በአገሪቱ የተከሰቱትን ህዝባዊ እንቅስቃሴዎች በሠላምና ዴሞክራሲያዊ በሆነ መንገድ ለመፍታት ባለመቻሉ በጠብ-መንጃ ኃይል ለታጠቀ ወታደራዊ  አገዛዝ አገሪቱን አሳልፎ በመስጠት ራሱም ጠፋ።

የአፄውን አገዛዝ የተካው በበኮሎኔር መንግሥቱ ኃይለማሪያም የተመራው ወታደራዊ ደረግ አገዛዝ ሥልጣን ይዞ በቆየበት አሥራሰባት አመታት ውስጥ "ኢትዮጵያትቅደም የሚል መርሆ በመጀመር "በሶሻሊዝም" ሥም ሁሉንም ኢትዮጵያዊ በድህነት አረንቋ ዘፈቀ። የህዝብ ኃብትንና ንብረትን ወርሶ የመንግሥት አደረገ። ለአገዛዙ አስጊና ተቀናቃኝ ወይም የተለየ  አስተሳሰብ ያላቸው መሰለው የታዩትን ንፁሃን ዜጎች በተለይም የተማረውንና ለዚያች አገር ሁለንተናዊ ዕድገት ይንገበገብና ይቆጭ የነበረውን ወጣቱን ትውልድ "ቀይ ሽብር" በሚል አረመናዊ ጭካኔ ገድሎታል። አስሮታል። የተረፈውንም ለአዕምሮና ለአካለ ሥንኩልነት፥ ለስደት ዳርጎታል ። በአጠቃላይ ይህ ፋሽስታዊ አገዛዝ በአገሪቱ አራቱም ማዕዘናት የሽብርና የሰቆቃን መዓት አወረደ ። የአገሪቱም ኢኮኖሚ ወደአዘቅት እንዲወርድ በማድረግ ህዝቡ ለረሃብ፥ለከፋ ድኅነትና ችግር እንዲጋለጥ አደረገ ።  ይህን የመሰለውን አስከፊ ወንጀልና ሽብር ሲፈፅም የነበረው  በአገር ሉዓላዊነት ሥም ነበር። ይህም አገዛዝ በበኩሉ ከሱ ለባሰ ዘረኛና አምባገነን ቦታውን ሊቅ ተገደደ ፡፡

ደርግን የተካው የኅወሃት/ኢህአዴግ አገዛዝ በኃይል የሚንልክን ቤተመንግሥት ከተቆጣጠረ በኋላ በአገራችን ታሪክ ለመጀመሪያ ጊዜ ፥ በዘርና በጠባብ ብሔርተኝነት ላይ የተመሠረተ ፖሊሲን በመንደፍ የአንድን ቡድን አምባገነንነት አንግሷል። በአገዛዙ የአስተደዳር መዋቅሮችና በአያሌ የማምረቻና የማከፋፈያ ድርጅቶች፥ በሙያ ማህበራት፥ በሲቪክ ድርጅቶችና በኃይማኖት ተቋማት ውስጥ ሳይቀር፥ በርካታ ቁልፍ የሥልጣንና፥  የኃላፊነት ቦታዎችን ፥ በካድሬዎቹና በአባሎቹ እንዲያዙ አድርጓል ። የመከላከያ፥ የፖሊስና የደህንነት ተቋሞቹ፤  በተለይ በሠራዊቱ በኅወሃት፥ ተዋጊ በነበሩ ታማኝ አባላቱ ዕዝ ቁጥጥር ሥር እንዲሆን መደረጉ የሚጠያይቅ አይደለም ። ኢትዮጵያም በታሪኳ ለመጀመሪያ ጊዜ  የመንግሥት አውታሮቸ ብቻ ሳይሆኑ የሲቪክ ድርጅቶቸ ኃላፊዎቸ ሁሉ ከአንድ ብሔር በተውጣጡና የአገዛዙ ደፊፊና አባል በሆኑ ግሽሰቦኘ ቁጥጥር እንዲሆኑ ተደረገ ፡፡  በዚህም የተነሳ በማንአለብኝነትና በፈላጭቆራጭነት የኢትዮጵያን ሉዓላዊነትና እስትራቴጅካዊ ጥቅም፥ በዘለቄታዊ መልኩ እየጎዳ፥ ሠላምና መረጋገትን እያራቀ ፥ ኢትዮጵያዊነትን በፅኑ እያዳከመ ይገኛል። በመለሥዜናዊ የሚመራዊ ጎጠኛ አገዛዝ ካለፉት አገዛዞች በከፋና በረቀቀ ዘዴ የአገዛዙን ዕድሜ ለማስቀጠል በአገሪቱ በመላ የዘር ፖለቲካ እሳት በመጫር፥ አንዱን ዘር፥ ከሌላው ጋር ይሁነኝ ብሎ በማጋጨትና ደም በማቃባት፥ የብዙ ሠላማዊ ሰው ህይወት እንዲጠፋ ፥ የተፈጥሮ ኃብትና ንብረት እንዲወድም፥ የዱር አራዊት ጭምር በእሳት እንዲጋዩና ወደጎረቤት አገሮች እንዲሰደዱ ጭምር አድርጓል። ዛሬም እንደገና ህዝቡን ለከፋ ድህነት፥ ረሃብና በሽታ ፥ እንዲሁም ለድርቁርና ዳርጓል።

በዘር ላይ የተመሰረተ ፖለቲካን ፥ የንፁሃን ዜጎችን መበት መረገጥን ፥የኢትዮጵያን ምሁራን ከሥራ መባረርን ወዘተ  የተቃወሙ አገርወዳድ የኅብረተሰቡ ክፍሎችን በጅምላ በመጨፍጨፍ፥ በተናጥል በመግደል፥ በማስርና በማሳደድ፥ ህገሪቱን ባዶዋን እያስቀራት ነው ። ለባዕዳንም ተንበርክኮ የእነርሱን ጥቅም አስጠባቂነቱን ብቻ ሳይሆን የሕዝብ ጣላትነቱንም  በሁለተናው መልኩ እያስመሰከረ ይገኛል ።በዚህም ጠባዩም፥  ለፍትህና ለዴሞክራሲ ፥ለዕኩልነትና ለአንድነት፥ በአገራችን ጦርነትም ሆነ የጦርነት አደጋ በማያዳግም ሁኔታ እንዲወገድ፥ ዘላቂ ሠላምና መረጋገት እንዲሰሡፍን ፥ኢትዮጵያዊያን በእኩልነትና በወድማማችነት መንፈሥ አንድነታቸውን እንዲያጠናክሩ፥ የብሔር ብሔረሰቦች መብት የተረጋገጣባት፥ የሰው ልጆች መሠረታዊ መብቶች የተከበሩባት፥ በነፃ ምርጫና በዴሞክራሲያዊ ሥርዓት የምትደዳር፥ የህግ የበላይነት የሰፈነባት፥ አገር እንድትሆን የሚታገሉ፥  የዴሞክራሲያዊ ኃይሎችን መሪዎችና የድርጅት አባላትንና ደጋፊዎቻቸውን ያሳድዳል ይረሽናል ያስራል ደብዛቸውን ያጠፋል።
የኅወሃት/ኢህአዴግ አገዛዝ የዴሞክራሲና የሠላም ጠንቅ በመሆን ሌሎች ተቃወሚ  ድርጅቶች በአገራቸው ምድር እንዳሻቸው ተደራጅተውና በነፃ ተዘዋውረው ዓላማቸውን ለህዝቡ አስረድተው በሠላማዊ የፖለቲካ መድረክ እንዳይሳተፉ አድርጓል።የግድያ የድብደባ ፥አፍኖደብዛን የማጥፋት፥ ሌሎችንም የኃይል እርምጃዎችን እየወሰደ፥ ነፃና  ዴሞክራሲያዊ ምርጫን በማካሄድ ሥም የምርጫ ቧልት እያካሄደ ያለበት ሁኔታ ውስጥ ነው ዛሬ የምንገኘው።

በአጠቃላይ የችግሮቻችን ምንጭ የሆነው የኅወሃት/ኢህአዴግ አገዛዝ  የጦር የፖሊስና የደህንነት መንግሥታዊ መዋቅሮች መከታ በማድረግ ፥ የኢትዮጵያ አንጡራ ሀብት የሆነውን ፥ የብዙሃን መገናኛ፥ የመንግሥት የፋይናስና የቁሳቁስ ኃይል ወዘተ ለጠባብ ብሔርተኛ ቡድኑ የጥፋት ዓላማዎቹ ማራመጃ እየጠቀመባቸው ይገኛል ። ይህ  ቡድን ሥልጣን ከያዘ ጀምሮ አካሄድኩ ያላቸውን ሶስት ዙር የምርጫ ሂደቶች ፥ ከዳር እስከዳር አዘገጃጀታቸውንና አካሄዳቸውን በመቆጣጠር፥ ይዘታቸውንና የመጨረሻ ውጤታቸውንም እጅግ አዛብቷል ። በማጭበርበርና በኃይል ጭምር ተጠቅሞ የምርጫዎቹ ውጤቶች በትክክል እንዳይታወቁ አደናቅፏል። በተለይም የግንቦት 1997 ዓ.ም. ምርጫም ውጤቱ፥ ሃቁ ታውቆ፥  በምርጫው አማካይነት የተገለጠው የህዝቡን ፍላጎት፥ እንዳያፀባርቀ በማድረጉ ፥  እነሆ ዛሬምአገሪቱን ለከፍተኛ አደጋ ፥ ህዝቧን ደግሞ ለቀውስ ዳርጓል ።
እስከዛሬ ተደረገዋል የተባሉት ምርጫዎች የፍሬቢስነታቸውም ዋናው ምክንያት ክምርጫና ከህገመንግሥት ቀድሞ በሀገሪቱ ለዴሞክራሲ የተመቻቸ ፥ ሁሉም የፖለቲካ ኃይሎች በአቻነት ሊወዳደሩ የሚችሉበት፥ አመቺ ሁኔታ እንዲኖር ባለመደረጉ ነው ።ይህንንም አይን ያወጣ ማጭበርበር ፥ ሸፍጥና፥ በማንአለብኝነት የሚካሄደውን ሸብር፥ በታዛቢነት የተሳተፉ ዓለምአቀፍ ታዛባዎች ጭምር ያረጋገጡት እውነታ ነው ።

## 2. አገራችን በፖለቲካ ቀውስ ተዘፍቃ ፍትህ ርትዕና የህግ የበላይነት ጠፍቶባት የሠላም መንገዱም ተወሳስቦባት... የምትገኝበት አስቸጋሪ ሁኔታን በአጭሩ::

የአገራችን ችግሮች ከጊዜ ወደጊዜ እየተቆለሉና እየተባባሱ መጥተው ዛሬ ትልቅ ተራራ አክለዋል ፡፡ ኢትዮጵያን ዛሬ ከየትኛውም አቅጣጫ ለሚያየት፥ ጎልቶ የሚታየውና የሚነገረው፥ ይኸው የተዘፈቀችበት ቀውስና ችግሯ ብቻ ሆኗል፡፡
የአገራችን ገዥዎች ለአገሪቷ ችግሮች በሠላማዊና ዴሞክራሲያዊ መንገድ፥ መፍትሄ ከመሻት ይልቅ፥ ቸግሯቿ የበለጠ እንዲበባሱና እንዲያመረቅዙ ፥ ሠላም፥ መረጋትና ብሔራዊ ዕርቅ ፥ በኢትዮጵያ ምድር እንዳይሰፍን፥ በህዝብ መካከል የጥላቻ ሙሹ እየደረደሩ፥ የጦርነት ከበሮን ጠዋት ማታ ሲደልቁ ይታያል ፡፡
በሌላ በኩል ደግም በአገሪቱ ውስጥ የፖለቲካ መረጋጋት እንዲፈጠር፥ ሕዝቡም አስተማመኝ ሠላምና ፀጥታ አግኝቶ ያለስጋት ለመኖር እንዲችል፥ የዳኝነት ተቋሞች ነፃ ሆነው የሚሠሩበት የህግ የበላይነት የተረጋገጠበት ሁኔታ እንዲፈጠርና፥ ህዝቡም በህግና ሥርዓት መኖር ላይ እምነት እንዲያድርበት ለማድረግ እንዲቻል፥ አፍቃሬ ሠላም በሆኑና፥ ለዴሞክራሲያዊ ሥርዓት የሚታገሉ ኢትዮጵያዊ ተቃዋሚ ኃይሎች በተናጥልም ሆነ በኅብረት በርካታ ጥረቶች ተደርገዋል ፡፡ሆኖም እስከዛሬ የተደረጉት ጥረቶችን ሁሉ በማምከን ኅወሃት/ኢህአዴግ የሠላምና የዕርቅ መሰናክል ሆኖ ቆይቷል፡፡ በኅወሃት/ኢህአዴግ የሚመራው ቡድን የኢትዮጵያን ህዝብ ማህበራዊና ኢኮኖሚያዊ ችግሮች ሊያስወግድ ቀርቶ አብዛኛዎቹን እያባባሳቸው ይገኛል፡፡ አገሪቱ ያለችበት የትምህርት ዕውቀትና ቴክኖሎጅ ኋላቀርነት አሳዛኝ ሆኖ ሳለ ፥ ይባስ ብሎም፥ የተማረው የሰው ኃይል ፥ በሥርዓቱ እየተማመረረና ህይወቱን ከአደጋ ለማዳን ሲል፥ በብዛት ሀገሩን እየለቀቀ በመሰደድ ላይ ላይ ነው ፡፡ <u>በሀገሪቱ ውስጥ የህግ የበላይነት፥ የፍርድ ቤቶችም ነፃነት፥ ባለመኖሩ፥ ዛሬ ኢትዮጵያ ውስጥ ህግና ሥርዓት፥ ከተባለም አምባገነን ገዥዎችን በፈተተቻው ፥ ህዝቡን የሚገዙበትና የሚነዱበት፥ ለእነርሱም የተመቻቸ፥ አማቂ፥ ህግና ፥ሥርዓት ነው ያለው ፡፡</u>
ዛሬ በአገራችን ሠላምና መረጋገት የለም ፡፡ የኅወሃት/ኢህአዴግ አገዛዝ የተለየ አመለካከት ያላቸውን የፖለቲካ ኃይሎች፥ የሲቪክና የሙያ ማህበራት፥ የሰብአዊ መብት ተሟጋች ድርጅቶችንና የኃይማኖት ተቋማትን፥ ነፃ ጋዜ አሳታሚዎችንና ጋዜጠኞችን፥ በህገ ወጥነት ፈርጆ አግዷል ወይንም አፍርሷል፡፡ መሪዎቸቻውንም ሲያሻው ይገድላል፡፡ ያለፍርድ ቤት ትዕዛዝ ያሥራል፡፡ አገር ለቀው እንዲሰደዱ ያደርጋል ፡፡ወንጀለኞችም ናቸው በሎ በመክሰስ ፥በሚቆጣጠራቸው የሥም ፍርደቤቶች አማካይነት፥ ለረዥም ጊዜ እሥራት ይዳርጋል፡፡ አለዚያም ከአቅማቸው በላይ በሆነ የገንዘብ ክፍያ ይቀጣል ፡፡ በተለይም የህዝብ አለኝታና የአገሪቱ የወደፊት ተስፋ የሆነውን ወጣቱን

ትውልድ በጠላትነት ፈርጆ " ወጣት ቦዘኔ" የሚል ተቀፅላ በመለጠፍ ይረሽናል ። ያግዛል። ያሳድዳል ። በአጠቃላይ አገዛዙ ከህዝብ ጋር ሆድና ጀርባ ሆኗል። የህዝብ ጠላትነቱም የማይደበቅበት ደረጃ ደርሷል።

እስከዛሬ በአገራችንያየናቸው ገዥዎች ሥልጣንና ዕውቀትን አቀናጅተው የፖለቲካ አመለካከት ልዩነቶችን እንደፀጋ ተቀብለውና አቻችለው የተለየ ሃሳብና አመለካከት ካላቸው ወገኖች ጋር ሠላምና ዕርቅ በማውረድ በመከባበር አብረው መሥራት አልፈቀዱም /አልቻሉም። ዛሬም እንደትናትናው የፍርድ ቤት ትዕዛዞች አይከበሩም። ከተበዳይ ይልቅ ÷ የበዳይ መብት ÷ አገርና ህግ ነው ያለው ። በፖለቲካው አስተዳር ላይ ያሉት ገዥዎች÷ ከላይ እስከታች ድረስ ÷ፈላጭና ቆራጮች ናቸው ።<u>በአገራችን እስከዛሬ የተለዋወጡት አሁንም በህዝብ ላይ÷ በኃይል ተጭኖ ያለው÷ አምባገነናዊ አገዝዝ ነው።</u> ጉልበት ያለው ተቃናቃኞቹን ሁሉ በኃይልና በጦር አቾንፎ÷ በህዝቡ ጫንቀ ላይ ቂጢጥ ብሎ÷ እንዳሻው ለህግና ለሥርዓት ሳይገዛ÷ እሱም ቀኑ ደርሶ በተራው÷ በኃይል እስከሚወገድ ድረስ÷ ህዝቡን ደፍጥጦ ሲገዛ ይቆያል ። በታሪካችን ያየናቸው የአገዛዝ ሥርአቶች የሚለያዩት÷ መራርነታቸውን ለመሸፈን በሚጠቀሙባቸው የማስመሰያ ሥልቶቻቸው ብቻ ነው።

## <u>3.የኅብረት ግንባርአሥፈላጊነት÷ ከሠላምና ብሄራዊ ዕርቅ ጋር ያለው ግኑኝነት</u>

በአንድ አገር ያለው ፖለቲካ ካልሠከነ ሠላም አይኖርም። ሠላም ከሌለ ደግሞ አጥጋቢ ዕድገትና ልማት ለማግኘት መቻል ጨርሶ አይታሰብም ። ሠላም ማለት ደግሞ የትጥቅ ፍልሚያ አለመኖር- የጥይት ተኩስ አለመሰማት ብቻ ተደርጎ ሊወሰድ አይገባም። እኛ ሠላም ስንል÷ ችግሩ የሚመለከታቸው ህዝቦች አዕምሮ÷ ጭንቀት÷ ሥጋትና ፍርሃት÷ እንዲሁም ወደግጭት ሊያመራ የሚችል÷ የጠላትነት ሰሜትና ጥላቻ ተወግደው÷ ዕርቅ ወርዶ÷ መልካም ግኑኝነትም ተፈጥሮ÷ በነፃ ማሰብና በነፃነት መኖር መቻል ማለት ነው ። በህዝብ ውስጥ ጭንቀትና ፍርሃት ካለ ሠላም የለም ። ያለምክንያት አይደለም ጦርነቶች በሰው ልጅ ዓዕምሮ ውስጥ ነው የሚፈጠሩት የሚባለው። ስለዚህ ሠላምም የሚፈጠረው በቅድሚያ የህዝቡ ዓዕምሮ ከጥላቻ ÷ከጠላትነት ሥሜት÷ ወደግጭት ከማምራት ሃሳብና ዘንባሌ ሲላቀቅ ነው ። አንድ ዜጋ በሙሉ ልቡ ተረጋግቶ ለልማት÷ ለዕድገት ሥራዎች÷ለትምህርትና ለምርምር አይተጋም። አንዲት ሀገር ሠላም ከሌላት ደግሞ ጤነኛ ዜጋም ለማፍራት አትችልም ። አገር እንደ አገር እንድትለማ ÷ሌሎች አገሮች የደረሱበት የዕድገት ደረጃ ላይ እንድትደርስ ከተፈለገ ÷ በቅድሚያ የአገሪቱ ፖለቲካ መስከንና መረጋገት አለበት። ዘላቂ ሠላምም መሥፈን ይኖርበታል።

<u>እስቲ ዝቅ ብለን ደግሞ ይህ እንዴት ሊሳካ ይችላል የሚለውን እንመልከት:-</u> የአገራችን ፖለቲካ አለመስከንና አለመረጋገት÷ የሠላም መጥፋት ያስከተለው ችግር÷ በአገራችን ጂኦግራፊካዊ ክልል ብቻ ተወስኖ የሚቀር ሳይሆን በገሃድ እንደታየው የአፍሪቃን ቀንድ በሙሉ የሚያተራምስ ሆኖ

ቆይቷል ። ዛሬም ይኸው ክስተት በአገዛዙ እርምጃዎች አማካይነት በተጠናከረ መልኩ ተባብሶ ይገኛል። ኢትዮጵያ በአፍሪቃ ቀንድ ባላት እስትራቴጂካዊ አቀማመጧና ታሪኳ የተነሳ ፥ በተጎራባችዋና በአጠቃላይም በአፍረካ አህጉር ላይ ጫናዋ ትልቅ ነው ። በአገሪቱ የፖለቲካ አለመረጋገት በመኖሩ ወይንም ሠላም በመጥፋቱ- የተነሳ ከአጎራባቾቿ ከኬንያ፥ ከሱዳን፥ ከሱማሊያና ከጂቡቲ ጋር በመከበባር ላይ የተመሠረተ መልካም ጉርብትናና ግኑኝነትን መሥርታ ለመኖር አልቻለችም ። የህገራችንንም ብሔራዊ ጥቅም ለማስከበር እንዳዳገተን ነው ያለነው ። ከዚህ ቀውስ ለመላቀቅ ያለጥርጥር ሠላም ያለጥርጥርያስፈልጋል ። ዕውነተኛ ሠላምና ዕርቅን ለማውረድ ደግሞ የሰብዕጉ የግድ ይላል ። ይህን ተልኮ ለማሳካት ደግሞ የኅብረት/የአንድነት አስፈላጊነት እሙን ነው ። በእውን እንደሚታየው ፥ ለአገራችን ፖለቲካ ደንቃራ ፈጥሮ ያለው ኅወሃት/ኢህአዴግ ለሠላማዊ መፍትሄ ፈቃደኝነቱን መንሳቱ ብቻ ሳይሆን ፥ አንዳንድ ተቃዋሚ ነን በሚሉ ድርጅቶች መካከል በመተማመንና በመፈቃቀድ ላይ የተመሠረተ፥ አገርን ከጥፋት ለማዳን በሚደረገው ትግል የጋራ የሆነ ራዕይ አለመያዛቸው አንደኛው ከፍተኛ ችግር ነው ። በተቃዋሚዎች ዙሩያ ፥ በብሔራዊ አጀንዳ ላይ የተመሠረተ፥ የኅብረት/የአንድነት ግንባር በመፍጠር በጋራ ቆመውና ተፋልመው፥ በሥልጣን ኮርቻ ላይ ያለውን፥ አጥፊነቱ የተረጋገጠና ከሥልጣንም መወገድም ያለበትን፥ የገዥ ቡድን፥ ለመጣል በሚደረገው አገርንና ህዝብን የማዳን ትግል በሚፈለገው መጠን ለመተባበር አለመቻሉ የፈጠረው ትልቅ መሰናክል ነው ።

የኢትዮጵያ ዴሞክራሲያዊ ኃይሎች (ኢዴኃኅ) ከተመሠረተ በኋላ ከነበረው የወራት ጊዜ በስተቀር - ኢትዮጵያዊያንን አደራጅተውና አስተባብረው፥ የሚታገሉና የሚያታግሉት ተቃወሚ ኃይሎች፥ እስከዛሬ አንድ ላይ በመሆን ኃይላቸውን አስተባብረው ፥ በአንድ ላይ አለመቆማቸው፤ ህዝባዊ መሠረትና ድጋፍ የሌለውን፥አምባገነኑ የመለሥዜናዊ ቡድን፥ ተዘራፍጦ በሥልጣን ላይ ለመቆየት ችሏል። ያለጥርጥር ለዚህም ሁኔታ መፈጠር ተጠያቂዎቹ ኅብረት እንዳይፈጠር መሰናክል የሆኑ ወይንም ኅብረት ከተፈጠረ በኋላ ኅብረቱ ተጠናክሮ እንዳይቀጥል የሚያደረጉት ተቃሚ የፖለቲካ ድርጅቶች ናቸው ። ይህ ሁኔታ ደግሞ ብዙሃኑ አገር ወዳድ ኢትዮጵያዊ ዜጋ ለአገራዊ ትግሉ ሊያበረክት የሚችለውን ሁለገብ አሰተዋፅኦ፥ በተቀናጀ መልኩ ለብሔራዊ ትግሉ መጠናከሪያ ሊያውል የሚችልበት መንገድ እስካሁን ድረስ በቅጡ እንዳይመቻቸ አድርጓል ። ውጤቱም ለአገር ቤት ትግሉ በድጋፍ ሰጭነት ሊያገለግል የሚችለው የውጭው የትግል እንቅስቃሴ፥ ዛሬም ከጠባብ የድርጅትና የቡድን ስሜት ተላቆ፥ በጋራ አገራዊ ራዕይ ዙሩያ፥ ኢትዮጵያዊያኑ ዕውቀታቸውን ፥ ኃይላቸውንና ገንዘባቸውን አስተባብረው እኒዲኅዙ ለማድረግ አለመቻሉ ብቻ ሳይሆን መኅዝ ። አገራዊ ትግሉ ለድል እንዲበቃ በውጭ ያለው ኢትዮጵያዊ የበኩሉን ፥ሊያደርግ የሚችለውን ሁሉ እንዳያደረግ ፥ጠንካራና የማይበገር የኅብረት ግንባር በማቋቋም ለማስከበርና ጥረቶቹን ለቕስቀጠል፥ ለማስቻልም ጭምር ነው ። አንዳንድ በተቃወሚነት የተሰለፉ የድርጅቶች መሪዎችም ቢሆኑ በተገኘው አጋጣሚ በየህዝባዊ መድረኩ በአደባባይ ፥ ያለውን አገዛዝ ሲያወግዙና ሲቃወሙ ቢደመጡም ፥ የግል ወይንም የድርጅቶቻቸውን ዝናና ክብር፥ ከአገር ጥቅምና ችግር በማስቀደም፥

እርስ በርሳቸው ከመወነጃጀል፥እንዲያውም መለስተኛ ልዩነቶቻቸውን ከማጉላት ታቅበው፥ አገር ወዳዱን ኢትዮጵያዊ አስተባብረው፥ ለማታገል አልቻሉም ። ከዚህ ጠንካራ የአንድነት ኃይል መፈጠር፥ ሊከተል የሚችለውን የዓለም አቀፉን ኅብረተሰብ ከበሬታም ለማግኘት አልቻሉም ። ይህ ጉደለታቸው ደግሞ ጠንካረ የአንደነት ኃይል በመፍጠር ሊከተል የሚቸለውን የዓለም አቀፉን ኅብረተሰብ ከበሬታም እንዳየገኝ ከፍተኛ አሰተዋፅኦ አበርክቷል፤፤ በእውነትም ደግም የለጥርጥር ሁሉንም ጎድቷል፤፤ ሰለሆነም ለኅብረትም ሆነ ለሠላምና ዕርቅ ፥ለአገርና ለህዝብ ከተባለ፥ በድርጅቶች መካከል ያለውን ልዩነቶች አቻችሎ ፥ ለውይይትና ለገንቢ ትችት ራስንና ድርጅትን ዝግጁ አድርጎ፥ አብሮ መታገለን ይጠይቃል።

የትግሉን ጊዜ ባለማስረዘም የህዝቡን የሥቃይ ጊዜ ለማሳጣር ፥አገራችን ከገባችበት ማጥ እንድትወጣ ለማድረግ ፥በድርጅቶች መካከል ሠላም፥ መግባበትንና ዕርቀን ፈጥሮ፥ በአንድ ጠንካራና ሠፋ ያለ፥ አገራዊ የኅብረት ግንባር ሥር ፥አሁንም ተቃዋሚዎች መሰባሰብ ይኖርባቸዋል። ይህንን ዕውን ለማድረግ ደግሞ ብሔራዊ ራዕይን ያነገበ፥ አስተዋይነትን፥ ቀናነትንና ገና ከጅምሩ የተቀዳጀ ድርጅት ፥ቀዳሚነቱን መውሰዱ የማይጠበቅ አይደለም ። ለአንድነትና ለዴሞክራሲ የቆሙ ኃይሎች በኅብረት መሰባሰብና መታገልን፥ እንደመርሆአቸው አድርገው መከተል የሚገባቸው መሠረታዊ ጉዳይ መሆን ይኖርበታል ። በኅብረት መሥራት ለረጅሙ ለአገራችን እስትራቴጂካዊ ዕድገትና ግንባታ ፥ ሁለንተናዊ የሆነ መንገድን የሚከፍት በጎ ተግባር ነው ። የተለያዩ የኅብረተሰቡ ክፍሎች ፥ የየራሳቸውን ጥቅምና ፍላጎት በተሻለ ይወክሉናል የሚሏቸው የፖለቲካ ኃይሎች፥ ሥፍራ ሲኖራቸው ነው ፥ ለፖለቲካው ሥርዓቱ ድጋፍ የሚሰጡት። የዴሞክራሲ አድማሱ የሚሰፋው። በዚህ መልኩ ነው አሳታፊነቱ የሚረጋገጠው። ይልቁንም ችግር የሚፈጠረው ፥አንድ ወይንም ጥቂት ድርጅቶች፥ ራሳቸውን ሥልጣን ላይ ለማውጣት፥ እሽቅድምድም ውስጥ ሲገቡና፥ የሕዝቡን ባለሥልጣንነት በተግባር ተቃውመው ሲገኙ ነው ። በአጭሩ ድርጅቶች የሕዝብ የትግል መሳሪያ ከመሆን ፈንታ ህዝቡን ተክተው ከእኔ በላይ ላሳር ብለው በህዝብ ቦታ ቆመው የሕዝብን ሥልጠን በእጃቸው ለማስገባት ከሞከሩ ለህዝብ መፍትሄ መሆናቸው ቀርቶ ለሠላም ለዕኩልነትና ለዴሞክራሲና ለአንድነት ጠንቅና በሽታ ይሆናሉ ።

የአንድ አገር ዕጣ የሚወሰነው በህዝቡ እንደመሆኑ መጠን በኅብረትግንባር መፈጠር ከፍተኛ ዕምነት ያለው ሕዝብ ለድርጅቶች(ለኅብረትግንባር) መጠናከርና መድከም ራሱን የቻለ አሰተዋፅኦ አለው። ስለሆነም ህዝቡ በፖለቲካው መስክ ሚናውን አሳልፎ ለድርጅቶች ሳይሰጥ መታገል ይኖርበታል።

ህዝቡም ለጥቅሙ የቆሙና የሚታገሉ የፖለቲካ ኃይሎችን በሁሉም መስክ እየደገፈ- እየበረታተ- እየወቀሰና እየመከረ የኅብረት ጥሪውን በራሱ ተሳትፎ እያጀበ ከታገለ ውጤቱ ፍሬአማ ሊሆን ይችላል ። ታጋይ ድርጅቶች በኅብረት ተሰባስበው፥ ታግለውና አታግለው፥ የኢትዮጵያ ህዝብ ካለበት የባርነት አገዘዝ ፥እንዲያወጡት ደጋግሞ ተማፅኗል። ዛሬም እንደትናትናው ይህ ሕዝብ ለነፃነቱ ክቡር የህይወት መስዋዕትነት እየከፈለ የሚያታግለውንና ትግሉን አስተባብሮ የሚመራውን መሪ ድርጅት/ኅብረት ይሻል ። የይድረሱልኝ ጥሪውንም በጩሁት እያሰማ ይገኛል። አሁን ባለው

የአገራችን ተጨባጭ የፖለቲካ ዕውነታም ዘላቂ ሠላምና መረጋገትን ፈጥሮ ለዕኩልነት ላይ የተመሠረተች አገርን ለመገንባት በኀብረት ተሰባስቦ ከመታገል ውጪ ሌላ አማረጭ ለማቅረብ አስቸጋሪ ይሆናል። በአገራችን ተጨባጭ ሁኔታ፥ አንድ ድርጅት የቱን ያህል ለኢትዮጵያ ብቸኛ ራዕይ ያለው ቢሆንም፥ ብቻውን በአገራችንና በሕዝባችን ላይ የተቆለለውን፥ ትልቅ፥ ጋራን የሚያክል ችግር ፥በመናድ አገራዊ መፍትሔ ያስገኛል ማለት ቅዥት ነው ፡፡

## 4. ብዙሃኑን ያሳተፈ ትግል ለሠላምና ለብሔራዊ ዕርቅ የሚኖረው ሚና :-

ከላፉት የትግል ተሞክሮዎች ሥንነሳ ሕዝብን ለሥልጣን ለማብቃት በሕዝብ ሥም ሥልጣን ላይ ያለውን አገዝዝ በብረት ኃይል አቸንፎ በመጣል ብቻ የሚወሰን አይደለም። ሕዝቡ በተጨባጭ የትግሉ በላቤትነቱን እንዲያረጋግጥ በራሱ መሥዋዕትነትም ተሞክሮውንም እንዲያዳብር መደረግ ይኖርበታል ፡፡ ለዚህም ትግሉም ሆነ የመጨረሻው ድል፥ ከድርጅቶች እጅ ወጥቶ በሕዝብ እጅ መግባቱ ዋስትናው ብዙሃኑን ያስተፈ ሕዝባዊ ትግል መካሄድ ሲችል ነው ፡፡ ይህ እንዲሆን ከተፈለገ ፥ በዛሬይቱ ኢትዮጵያ ያልተበደ፥ ያልተገፋ ፥ዕምነቱና ማኀበራዊ ጥቅሙ ያልተነካ፥ የኅብረተሰብ ክፍል አለ ለማለት ስለማይቻል። ለሠላምና ለብሔራዊ ዕርቅ ጉባዔ ዕውን መሆን፥ ባለብዙ ፈርጅ በሆነው የኢትዮጵያ ትግል ውስጥ፥ የኃይማኖት፥ የዕድር፥ የዕቁብ ተቋማት፥ የሙያና የሲቪክ ማህበራት ፥ ወጣቶችና ሴቶች፥የፖለቲካ ድርጅቶች ወዘተ ሊሳተፉ ይገባል። የሠላምና ብሔራዊ ዕርቅ ጉባዔን መጥራት አንገባጋቢና ለነገ የማንለው የወቅቱ ብሔራዊ ግዳጃችን ነው ፡፡ ይህ ጥሩ ዓላማ፥ ጥራት ባለው ሃሳብና መርሆ ላይ ተመሥርቶ፥ ብቃት ባላቸው አንቀሳቀሰሾች አማከይነት ሊሰራበት የሚገባ ነው ፡፡ ከሁሉም በላይ ለሕዝባችንና ለሀገራችን ሠላምን ለማሥፈን አማራጭ የሌለው ተግባር መሆኑን ሁሉም አፅንኦት ሰጥቶ ሊገነዘበው ይገባል ፡፡ አገር የማዳን ተግባር መሆኑንም ሁሉም አገር ወዳድ ዜጋ ነኝ የሚል ሁሉ ሊያምንበትና ለተግባራዊነቱም ከዳር እስከዳር በመንቀሳቀስና መታገል ይኖርበታል ፡፡ ይህ ጉባዔም በአገራችን ዋና ከተማ በአዲስ አበባ፥ ዓለም አቀፍ ታዛቢዎች በሚገኙበት፥ መካሄድ ይኖርበታል ፡፡ ይህ የሠላምና ዕርቅ ጉባዔ፥ ቅድሚያ ሰጥቶ ከሚነጋገርባቸው ዋና ዋና ጉዳዮች አንዱ ፥አሁን በሥልጣን ላይ ያለውን የገዥ ቡድን ጨምሮ ፥ ሁሉንም የፖለቲካ ኃይሎች የካተተ ፥ የብሔራዊ የአንድነት የሽግግር መንግሥት ማቋቋም ሲሆን፥ የሩቅ ዓላማው ዘለቄታዊ ለሆነው ፥ ለአገሪቱ ብሔራዊ ጥቅም መሠረት ሊሆን የሚችል፥ ለአንድ ሰው የአንድ ድምፅ መርህ ላይ የተመሠረተ የመድበለ ፓርቲ ዴሞክራሲያዊ ሥርዓትን መሠረት ያደረገ ሲሆን ራዕዩን የሚመሠርተውም የአገሪቱ ህዝቦች ብሔራዊ የጋራ ጥቅምና የወደፊት ተስፋ በመጠበቅና በማረጋገጥ ላይ የተመረኮዘ ይሆናል ፡፡

4.የሠላምና የብሄራዊ ዕርቅ ጉባዔ ራዕይና ተልዕኮ ዘለቄታዊ ግብን በተመለከተ:- የሠብዕጉ ዋነው ራዕይ ለኢትዮጵያ ሕዝብ ዘለቄታ ያለው ሠላምና በመፈቃቀድ ላይ ተደላድሎ የቆመ ሀገራዊ ህላዌ

እስትራቴጂካዊና ብሔራዊ ጥቅምዋን ሊያስገኝና ሊያረጋግጥ የሚችል ዴሞክራሲያዊ ህገ-መንግሥትና የመድበለ ፓርቲ ፖለቲካ ሥርዓትን መመሥረት ነው ። የቅርብ ይሁን የሩቅ ዓላማው የኢትዮጵያን ሕዝብ አስተማመኝ የሆነ ሠላምና መረጋገት አግኝቶ የተፈጥሮ ሐብቱንና ዕውቀቱን በመጠቀም ሀገሩን እያለማና፥ እያሳደገ፥ ከጎረቤትና ከመሰል ሀገሮች በጋራ፥ በመከበባርና በመቻቻል ላይ የተመሠረተ፥ መልካም ጉልብትናና ግኑኝነት ፈጥሮ፥ በልማትና በዕድገት ጎዳና፥ የምትራመድ ኢትዮጵያን ዕውን ለማድረግ ነው ። አሁን በሥልጣን ላይ ያለው የኅውሃት/ኢህአዴግ አገዛዝ፥ ከፊሎቹን በህገ ወጥነት፥ ሌሎቹን ደግሞ በህጋዊነት ፈርጆ፥ ሀገ-ወጥ ናቸው የሚላቸውን፥ ለማጥፋት እያሰደደ፥ ጉዳት ሲያደርስባቸው ቆይቷል። ስለዚህም ነው በምርጫ ተሸናፊ የሆነውን የኅወሃት/ኢህአዴግን ጨምሮ "ለጊዚአዊ ብሔራዊ የአንድነት የሽግግር መንግሥት ምሥረታ" ጋብዘው የነበሩት አሁንም ቢሆን የወደፊቱን ችግር ለመቅረፍ እንዲቻል ኅወሃት/ ኢህአደግን የተቃዋሚ ኃይሎችን- የሲቪክና የሙያ ማህበራትን፥ የኃይማኖት ተቋማትን ወዘተ... ያቀፈ የተለያዩ የኅብረተሰቡ ክፍሎችን ፍላጎትና ሃሳብ በበቂ ሊወከልና፥ ሊገለፅበት የሚችል፥ አገራዊ ብሔራዊ ጉባዔ በመጥራት ፥ በኢትዮጵያ የወደፊት ራዕይ ላይ ከተወያየ በኋላ፥ ብሔራዊ የሆነ አጀንዳ በመቅረፅ፥ ብሔራዊ የሽግግር መንግሥት/የአንድነት መንግሥት ማቋቋም ይሆናል። የሽግግሩን መንግሥትለማቋቋም በዋናነት ሊቀርቡ ይገባል የሚባሉ አጀንዳዎችን በተመለከተ

1ኛ. የኢትዮጵያን ለአያሌ ዘመናት የቆየ የፖለቲካ ታሪክና ተመክሮ(ደግና ክፉን) እንዲሁም አሁን ያለውን በዘር ላይ የተመሠረተውን የኅወሃት/ኢህአዴግን አገዛዝ ፥እሱም እያስከተለ ያለውን፥ ብሔራዊ ጥፋት፥ በሚገባ መመርመር። የወደፊቱን የአገራችንን እስታራቴጅአዊ ራዕይ መንደፍ ።

2ኛ. የኢትዮጵያ ህዝቦች ሊኖራቸው የሚገባውን ሉዓላዊነትና ባለሙሉ ሥልጣን(እስከዛሬ ኃላፊነቱና ተጠያቂነቱ የእነርሱ የሆነ መንግሥት አግኝተው ስለማያዉቁ) እንዲሁም የሚመሰረተው መንግሥታዊ መዋቅር ቋሚ በሆነ ሠነድ(በህገመንግሥት ረቂቅ) ተቀርፆ የሚቀርብበትን ሁኔታን ማመቻት።

3. ለዘመናት በሁለተናዊ በይነገበርና ተባደል የኢትዮጵያን ዜግነትን፥ ኢትዮጵያዊነትን እያሰረፀ፥ የራሱ የሆነ መለያ እያገኘ፥ በጋብቻ ፥በኃይማኖትና በባህል፥ በንግድና በማኅበራዊ ኑሮ-... ወዘተ እየተሳሰረ የመጣው ሕዝብ ኢትዮጵያዊነቱ መታወቂያው ሆኖ የተፈጠረው የጋራ ስሜትና ዕምነትም በጋራ የውጪ ወራሪንም ለመቋቋም አስችሎት የቆየውን ኩሩና ጀግና ህዝብ ለመነጣጠል በዘር ፖለቲካ አማካይነት የተቃጣባትን የብጥብጥትና የግጭት አደጋ ተቋቋሞ በእኩልነቱ ላይ የተመሠረተ፦
አንድነቱ የሚፀናበትንና ቀናን መንገድ መሻት።

4. በዜጎች ላይ በኅወሃት/ኢህአዴግ እየተካሄደ ያለው እመቃ ፥አፈና፥ ግድያና ወከባ፥ ያላንዳች ቅድመሁኔታ ቆሞ፥ ሰብዓዊና ዴሞክራሲያዊ መብቶች የሚከበሩበትን ሁኔታ ለመፍጠር እንዲቻል በረቂቅ ሕገ-መንግሥት ውስጥ ሰብዓዊና ዴሞክራሲያዊ መብቶችን በሚገባ ማካተት።

5ኛ.በኅወሃትና በኤርትራው ሻዕቢያ የተሣሣቱ ፖሊሲዎች የተነሳ የተቀሰቀሰው ጦርነት፥ ያስከተለውን ችግር፥ ከነመሻ ምክንያቶቹ መርምሮ፥ ይህ የኤርትራ ችግር አሁንም ዕልባት ባለማግኘቱ ዳግም ጥፋትና ጦርነት እንዳይከተል፥ በሠለማዊ መንገድ ዘላቂ መፍትሔ የሚገኝበትን ሁኔታ ስለመፍጠር ትልሞችን ማዘጋጀት።

6ኛ. የኅወሃት/ኢህአዴግ አምባገነን አገዛዝ የፕረስን ህግ በማውጣት ሥም ሃሳብን በነፃ የመግለጥ መብቶችን ነው ያቀበው። የህግና የፍትህ ሥርዓቱን በመቆጣጠር የዜጎችን መብት በሰፊው እየገፈፈ ነው ። ኅወሃት/ኢህዴግ የገፈፈውን በነፃ የመደራጀት መብት በማረጋገጥ የሙያ ማህበራት፥ በአጠቃላይ የሲቪክ ማህበራት በሙሉ እንዲሁም ነፃ ጋዜጠኞች ሊንቀሳቀሱ የሚችሉበትን ሁኔታ ስለመፍጠር።

7ኛ. በኅወሃት/ኢህአዴግ አገዛዝ ሥር ጠባብ የዘር ፖለቲካ መሠረት ባደረገ መንገድ የተደራጁትን፥ የጦር ኃይሉን ፥የፖሊስና የፀጥታ ክፍሎቹን ሙሉ በሙሉ፥ ከአንድ ብሔረሰብ ቁጥጥር ሥር አላቅቆ፥ በትክክል የሀገራቱን ጥቅምና ሉዓላዊነት የሚጠብቁ ተቋሞች ሊሆኑ የሚችሉበትን መንገድ መሻት።

ይህ የሰላምና ዕርቅ ብሔራዊ ጉባዔ ሲጠራ አገራችን ካለችበት ማጥ እንድትወጣ ለማድረግ በዘር ላይ የተመሠረተው ፖለቲካ እስካሁን ያስከተለውን ጠንቅ፥ብክለትና ጥፋት አስውግዶ፥ በአዲስ መንፈስና፥ በአዲስ ራዕይ፥ ለአገርና ለህዝብ በመጠቅም ሥርዓት ከመተካት አኳያ መሆን ይገባወል ።
ከጥንተ መሠረትም ከተለያየ ብሔር/ብሔረሰብ ስብሰብና ስብጥር የተገነባች ሕብረብሔራዊቲ አገር መሆኗን በግልፅና በማያሻማ ሁኔታ ማስረገጥ። ኦሮሞው-አማራው- ትግሬው-ጉራጌው-ገሙው-ወላይታው-ሲዳማው-ጌዲዎው- ቤናሻንጉል ጉሙዙ- አፈሩ አደሬው -ጊሚራው -ከምባታው-ሀዲያው ሌሎቹም ብሔር/ብሔረሰቦች የሀገሪቱ እኩል ባለቤቶች መሆናቸው ተረጋግጦ፥ እርስበርሳቸው በመተበባርና በመከበባር አብረው ሊኖሩ የሚያስችሏቸው የጋራ ጥቅሞች እንዳሏቸውም በትክክል ማሳየትና ማሰረዳት ያሻል።ከውስጥ የፈለቀ የማይቀረፈ ቅራኔ በኢትዮጵያ ብሔር/ብሔረሰቦች መካከል አለ እያለ ኅወሃት/ኢህአዴግ የሚያራግበውን በዘርና በቋንቋ እየከፋፋለ ኢትዮጵያን ለማዳከም የተጠቀመበትንና እስከዛሬም ያስቻለውን መሠረተቢስ ማጠየቂያውን

ሃሰትነት በሚገባ ማሳየት ያስፈልጋል ። ሠብዕኑ በሕዝቡ መካከል ሊኖር የሚገባውን በጋራ ጥቅሙ ላይ የተመሠረተ የጋራ ራዕይ በአፅንኦት ማረጋገጥ ይገባዋል ። የጎወሃትን አገር አፍራሽ ፖለቲካ ለውጦ በዜጎች መካከል ዕምነት መተባበርና መከበባር ሠላምና መቻቻል የሚሰፍንበትን ሁኔታ መፍጠር ከሠብዕኑ ብሔራዊ አጀንዳው አኳያ አንደኛው ሊሆን ይገባል ።

## 5.የሠላምና ዕርቅ ብሔራዊ ጉባዔን ለመጥራት ምን መደረግ አለበት?

ሀ. በኢትዮጵያ የወደፊት ዕድል/ራዕይ ያገባኛል የሚሉ በአገር ውስጥና በውጪ በህጋዊነትም ሆነ በህገወጥነት በጎወሃት አገዛዝ ተፈርጀው ያሉ የተቃዋሚ ኃይሎች፥ የሲቪክና የሙያ ማህበራት፥ ታዋቂ ግለሰቦች6 የአገር ሽማጊሌዎችና ባልቴቶች፥ ወጣቶች፥ የኃይማኖት መሪዎች ጭምር እርስበርሳቸው ሊያስተማምኗቸው የሚያስኗቸውን ዕርምጃዎች በጋራ ማከሄድና ይናርባቸዋል ። ለዚህም ሂደት በውይይት፥ በምክክር፥የጋራ አቋም ሊያስገኙ በሚያስችሉ ነጥቦች ዙሩያ መስማመት ይጠበቅባቸዋል ።

ለ. ጋዜጠኞች፥ የመገናኛ ብዙሃን፥ የከፍተኛ ትምህርት መምህራንና ምሁሮች(የአካዳሚ ሰዎች) የሙያ ማህበራት፥ የሠራተኛው ክፍል ፥አርሦ አደሮች፥ ወጣቶችና ሴቶች፥ እንዲሁም ሌሎች የኅብረተሰቡ ክፍሎች6 በአንድ ድምፅና በጋራ ዓላማ አገርን ከጥፋት ለማዳን ለሚደረገው ትግል የሠዕብጉን አስፈላጊነትና ወቅታዊነትን በተመለከተ አዎንታዊ ምላሽ ሰጥተው ሊደግፉትና ሊሳተፉበት ይገባል ። የዚህን ጉባዔ አስፈላጊነት ዓላማና ወቅታዊነት በመደገፍ ገንቢ ቅስቀሳና ፕሮፓጋንዳ ማድረግ የድጋፍ ሠላማዊ ሰልፎችን ህዝባዊ ስብሰባዎችን በአገር ውስጥና በዉጪ አገር በተከታተይ ማካሄድና ሠላም ወደዳ የሆነው የዓለም ማህበሰብ ለሠላምና ለዴሞክራሲ የምናደርገውን ያለሰለሰ ትግል እንዲያግዝ ተገቢውን የዲፕሎማሲያዊ ትግል ማድረግ ጉባዔውንም በገንዘብና በቁሳቁስ የሚረዱ መንግሥታዊና መንግሥታዊ ያልሆኑ አካላትን ድጋፍ ለማግኘት መጣር ያስፈልጋል ።

<u>ሐ</u> በተቃወሚ ጎራ የሚገኙ ምሁራን ለሠብዕኑ ስኬታማነት ዕገዛ ሊያደርጉ በሚችሉበት ምልክ የተዘጋጁ በአገራችን ተጨባጭ ፖለቲካዊ -ኤኮኖሚያዊ- ማህበራዊ-ባህላዊ ወዘተ ሁኔታዎች ላይ የታኮሩና የሌሎች ሀገሮችን ተሞክሮና ልምድ ያዛመዱ ጥናታዊ ፅሁፎችን በመረጃዎች እያስደገፉ እንዲያቀርቡ ማሳትፍና መጋበዝ ያስፈልጋል ።

መ. ገለልተኛ የሆኑ ዓለም አቀፍ ታዛቢዎች በሚገኙበት የሽግግር/ብሔራዊ የአንድትን ጊዛዊ መንግሥት ዕውን የሚሆንበትን ጉባዔ እንዲጋጅ ጥሪውን ማስተላለፍ ።

ሠ. ሠብዕጉ ሁሉን ያቀፈ(ማንንም የላገለለ) ዴሞክራሲያዊ መሆን እንዳለበት ማረጋገጥና ለዚህመን ከገዥው ፓርቲ ጎራም በዚሁ ሂደት ለመሳተፍ ፈቃደኛ የሆኑትን በማሰባሰብ ማሳተፍ ይገባል ::

## ማጠቃለያ

አገራችን እየተጓዘችበት ያለውን የጥፋት ጎዳነ ሥንመረምር ጎወሃት/ኢህአዴግ የሚያካሂደው በዘር (በብሔርተኝነት )ላይ የተመሰረተ የክልል ፖለቲካ÷ ሕዝብን ለዕርስ በርስ ዕልቂትና ፍጅት አየጋበዘና እያመቻቸ÷ ሀገርንም እያፈረራሰ መሆኑ÷ በገሃድ ይታያል:: ትናትና በሩዋንዳ በዞማሊያና በቦስንያ የተከሰተው ዕልቂት/አደጋ በጊዜና በአግባቡ መፍትሔ ካልተበጀለት÷ በኢትዮጵያ ፍፁም ሊከሰት አይችልም ማለት አዳጋች ነው :: ዛሬ የምናየውና በአገራችን ላይ ያንዣበበው በገዥው ቡድን አበጣባጭነት እስከዛሬ ተስማምተውና ተከበባ/ረውም በኖሩ ኢትዮጵያዊያን ብሔረሰቦች መካከል ሊነሳ የሚችል የርሰበርስ የመጨፋጨፍ አደጋ ነው :: የአገር አንድነት መሠረት የሆነው ሕዝብ -አንድነት÷  በአንድ አገር ውስጥ ከጠፋ÷ የሰማይን ያህል ሊርቅ ይችላል:: ሰለዚህ ኢትዮጵያሰ እንድትትፋ ማለትም ሕዝቧ በዘርና በኃይማኖት ተከፋፍሎ ጎጠኞች ያጠመዱት ፈንጂ አገርና ህዝብ እንዳያጠፋ አገር ወዳዱ ዜጋ አገርን የመታደግ ታሪካዊ ግዴታ ስለለበት ለአንዴም ለመጨረሻም በአገራችን ዘላቂን ሠላም ለማስፈን ለሠብዕጉ ዕውን መሆን ከመቸውም ጊዜ በበለጠ መታገል ይገባል ሀገርን ለማዳን  የሚደረገው ትግል ስኬታመ ሊሆን የሚችለው የአገር አንደነትን ከዴሞክራሲያዊ መብት ጋር አብሮም የሚካሄድ ትግል እስከሆነ ድረስ ብቻ ነው :: እኛ የምንመኛትና የምንታገልላት ሀገር ሁሉንም በዕኩልነት ለምታስተናግድ መሆን ይኖርበታል :: ይህ ማለት የትናት ወዲያውን የአፄውን ሥርዓት÷ የትናትናውን የመንግሥቱን አገዘዝ÷ የዛሬውን የመለሥን ዘረኛ አገዛዝ ÷ለማትደግም ሠላም÷ ዕኩልነት ÷ ፍትህና ዴሞክራሲ ለሰፈነባት ÷ ኢትዮጵያ መሆኑን ማረጋገጥ አለብን ::